## 14. የቅድመ ግብር ክፍያ አማዛጋገብ፣ ሪፖርት አቀራረብና የገቢ ሚከተላለፍ

1. በታክስ ባለስልጣኝት ስለሚፈረግ የቅድመ ግብር ክፍያ ሂሳብ አማዛጋገብ

ሀ) ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የተቀነሰ ታክስ የንግድ ትርፍ ግብር ወይም የቤት ኪራይ ገቢ ግብር አካል በሚሆኑ የታክስ ባለስልጣኝት የራሳቸውን ድርሻ ሲሰበስቡ በተለሚዷው የቀጥታ ታክስ ገቢ እንደ አግባብነቱ በ1102 ወይም በ1104/1103 በሚደበኛ ገቢነት ይማዝግባሉ፡፡

ለ) የታክስ ባለስልጣኝት ከራሳቸው ህጋዊ ገቢ ውጭ የሌሎች ታክስ ባለስልጣኝትን ድርሻ የሚበሰብበት ሁኔታ ሲያጋጥም በአደራ ሂሳብ ቁጥር 5026 መማዝገብ አለባቸው፡፡

ሐ) የገቢዎች ሚኒስቴር በታክስ ባለስልጣኝት ከሚበሰብ የቅድመ ግብር ክፍያ ጋር በተያያዘ ግብሩን ቀንሶ የሚያስቀረው ሰው እና ገቢውን የሚበሰበው የታክስ ባለሥልጣን ሂሳቡን የሚማዝገብበትን፣ ገቢው እና ከገቢው ጋር የተያያዘ አግባብነት ያለው ሚረጃ የገቢው ባለቤት ለሆነው የፌደራል ወይም የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር ታክስ ባለሥልጣን የሚላለፍበትን፣ ሪፖርት የሚዘጋጅበትና ለሚመለከታቸው አካላት የሚቀርብበትን የአሰራር ስርዓት በማዘርጋት ተፈጻሚ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

2. ግብር ቀንሰው የሚያስቀሩና ግብር የሚቀነስባቸው ሰዎች ሂሣብ አማዛጋገብ

ሀ) ማንኛውም በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 92 ግብርን ቀንሶ ገቢ የሚድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ሰው ዕቃም ሆነ አገልግሎት ሲገዛ እንዲሁም ሻጩ ዕቃም ሆነ አገልግሎት ሲያቀርብ አጠቃላይ የግዥውን ወይም የሽያጩን ሙሉ ዋጋ በሂሳብ ማዝገብ መማዝገብ አለበት፡፡

ለ) ዕቃውን ወይም አገልግሎቱን የሚዛው ሰው ወይም ድርጅት ሙሉ ክፍያውን እንደወጪ በመማዝገብ 2% /ሁለት በመቶ/ ከተከፋይ ሂሳብ ተቀናሽ ግብሩን በደረሰኝ ገቢ በሚድረግ ይማዝግባል፡፡ አማዛጋገቡም -

- ግዥ /ተከፋይ ሂሣብ /100%/ ............................. ደቢት
- ጥሬ ገንዘብ /cash (98%) ................................ ክሬዲት
- የቅድሚያ ግብር ክፍያ Withholding tax payable (2%) …. ክሬዲት

በሚድረግ ይሆናል፡፡

ሐ) የዕቃው ወይም የአገልግሎት አቅራቢም ሙሉ ሂሣቡን ተቀብያለሁ ሲል ደረሰኝ በማጠት ለ2% /ሁለት በመቶ/ ከተከፋይ ሂሣብ የሚቀነስ ቅድሚያ ግብር ከፈልኩ በማለት ገዥው በሚሰጠው ደረሰኝ መሠረት በቅድሚያ ግብር ክፍያ ይዞ በሂሣብ ማዝገቡ ያሰፍራል፡፡

በዚህም ማሰረት ፡-

- ጥሬ ገንዘብ (98%)......................................… ደቢት

